# ኢየሱስን መከተል



## ደቀ-መዛሙርት ማድረግ እና መንፈሳዊ እንቅስቃሴን መገንባት

ደቀ-መዛሙርት ማለት “ፕሮቴጌስ”/protégés/ ማለት ሲሆን ትርጉሙም ተማሪዎች ማለት ነው። ይኸዉም የኢየሱስ ተማሪዎችና ተከታቶች ሲሆኑ፤ የእርሱንም መንገድ በመከተል እርሱ የጀመረዉን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚያስቀጥሉና ደቀ - መዛሙርትን የሚያበዙ ናቸው። ይህንንም በማድረጋቸው ሰዎችን ለእርሱ ዳግም ምጽዓት የሚያዘጋጁ ናቸው። ስለሆነም ደቀ - መዝሙር በሁሉም የሕይወት ዙሪያ እርሱን ለመምሰል የሚያድግ አማኝ ነው።

መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚፈጠረው የኢየሱስ ተከታዮች በማህበረሰቡ ዉስጥ ገብተው በሽክምና በርህራሄ ወንጌል ሲሰብኩ፤ የህብረተሰቡን መንፈሳዊ ጥማት ሲያረኩ፤ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በመጋበዝና ደቀ-መዛሙርት በማድረግ እነርሱም በተራቸዉ ባላቸዉ ማህበራዊ ግንኙነትና ተጽዕኖ ሌሎች ደቀ -መዛሙርትን ማብዛት ሲችሉ ነው።

PETER ROENNFELDT

WWW.FOLLOWING-JESUS.COM
Amharic, Ethiopia

# ዲስከቨሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ

ስለ ኢየሱስ ያለን ዕውቀትና ልምምድ የቱንም ያህል ቢሆን ቀላልና ውጤታማ የንባብ ዕቅድ ሲሆን፡-

- ወዳጆች የኢየሱስን ታሪክ ለማንበብና ለማጥናት የሚገናኙበት ነው፤( የማርቆስ ወንጌል ጥሩ ጅማሮ ሊሆን ይችላል)
- አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ሊጸልይ ይችላል: “ጌታ ሆይ እባክህ ምራን ፤ አመሰግንሃለሁ !.”
- አንድን ታሪክ አንድ ጊዜ ብቻ በማንበብ ጀምሩ
- ከዚያም በመቀጠል እያንዳንዱን ታሪክ ሁለት ጊዜ በመድገም ከዚያ በኋላ ታሪኩን በራሳችን አባባል ደግመን እንናገረው፤

ያነበብነዉን ታሪክ የሚከተሉትን 5 ጥያቄዎችን በመጠቀም እንወያይበት:

1. በታሪኩ ዉስጥ ያገኘነው አዲስ ነገር ምንድነው?
2. ከታሪኩ ውስጥ ያስደነቀን ነገር ምንድነው?
3. ከታሪኩ ውስጥ ያልገባን ነገር ምንድነው?
4. ልንታዘዘው ወይም ተግባራዊ ልናደርገው የሚገባን ነገር ምንድነው?
5. በዚህ ሳምንት ለሌሎች ላካፍለው የምችለው ነገር ምንድነው?

- ደግመን የምንገናኝበትን ጊዜ መወሰን.
- አንዱ ለአንዱም መፀለይ፤ እንዲህ ብለን መፀለይ እንችላለን:

“ጌታ ሆይ ስለ ቃልህ እናመሰግንሃለን !እንድንከተልህ እርዳን! አሜን”

## ምክረ - ሃሳብ

- ክፍሉ ካልገባችሁ አትከራከሩ፤ ታሪኩን ደጋግማችሁ አንብቡ !
- ሌሎችም እንዲካፈሉ ጋብዙ.
- ለሁሉም ሰው ማስታወሻ አዘጋጁ.
- ሌሎችም ሌላ ቡድን እንዲመሰረቱ አበረታቱ.

## በድጋሚ ስትገናኙ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቁ ፡-

1. በሳምንቱ ዉስጥ ማንን አግኝታችሁ አካፈላችሁት?
2. ከዚህ የተማራችሁት 2 ነገሮች ምንድናቸው?

ክለሳ:

1. የተማርነዉን እውነት በሕይወታችን መተግበር ያለብን እንዴት ነው?
2. የተገነዘብነዉን እውነት ለሌሎች ማካፈል ያለብን እንዴት ነው?

ከዚያ በኋላ የሚቀጥለዉን ታሪክ ማንበብ ቀጥሉ!